## መግቢያ

የአማራ ክልል የተፈቀደላቸዉ ሒሣብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች ማህበር በሰኔ ወር 2006 ዓ.ም ሲቋቋም ካስቀመጣቸው ዋና ዋና አላማዎች ውስጥአባላት የሙያ ስነምግባራቸውን ጠብቀው እስከሰሩ ድረስ ከተለያዩ ሊደርሱባችው የሚችሉ ተጽዕኖዎችን በመለየትና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ መብታቸው እንዲከበር ማድረግ አንዱ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አባላት የሙያ ስነምግባራቸውን ጠብቀው የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ሁሉ እንዲወጡ ለማስቻል ተገቢውን ክትትል ማድረግና ጥፋቶች ሲከሰቱ ተገቢውን የእርምት እንዲወሰድ ማድረግ ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በባህሪያቸው የማይነጣጠሉ ናቸው ተብሎ ይታመናል፤ ምክንያቱም በየትኛውም የአለም ክፍል የሚገኝ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን መብቱ እንዲከበርለት ለመጠየቅ መጀመሪያ ግዴታዎችን አውቆ መተግበር የግድ የሚል ስለሆነ ነው ፡፡

በዚህ መሰረት የፌደራል እና የአማራ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተለያየ ጊዜ ያወጧቸውን የሙያ ስነምግባር ደንብ እና መመሪያዎችን መነሻ በማድረግ ሙያዊ ግዴታችን መወጣት ከኛ ከተፈቀደላቸው ሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች የሚጠበቅ ከመሆኑም በላይ ለእያንዳንዳችን ዘላቂ ጥቅምም የሚበጅ ይሆናል፡፡

ስለሆነም የማህበሩ አባላት በፌደራልና በክልል ደረጃ የወጡ የተለያዩ ተዛማጅ ህጎችን እንዲሁም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አክብረው እንዲሰሩ ለማስቻል ይህ የስነ ምግባር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

### 1. አላማ

አባላት የሙያ ስነ-ምግባራቸውን ጠብቀው የተጣለባቸውን ሃላፊነት በብቃት እንዲወጡ፤ በምላሹ አባላት ራሳቸው ብሎም ያደራጁት ማህበር በየትኛውም አካል እና መድረክ ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና መብታቸው ተከብሮ እንዲሰሩ ለማስቻል ነው፡፡

## 2.የስነ ምግባር መመሪያ

### መመሪያ አንድ

### ከአማራ ክልል የተፈቀደላቸው የሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች ማህበር ጋር በተያያዘ

1.1. አባላት የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አክብረው ሊንቀሳቀሱ ይገባል፡፡

1.1.1. አባላት ከማህበሩ የሚሰጣቸውን የስራ ሃላፊነት ተቀብለው በአግባቡ ማከናወን አለባቸው

1.1.2. አባላት በማህበሩ ወይም በተዋረድ ባሉ ቅርንጫፍ ማህበራት ለስብሰባ በሚጠሩባት ጊዜ በሰአቱ በመገኘት ወይም ህጋዊ ተወካያቸው እንዲገኝ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት አለባቸው

1.1.3. አባላት በማህበሩ የሚወሰኑ የገንዘብ መዋጮዎችን በወቅቱ መክፈል አለባቸው፡፡

1.1.4. አባላት ሌሎች በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የሰፈሩ ግዴታዎችን ባግባቡ መወጣት ይጠበቀባቸዋል፡፡

1.1.5.አባላት የማህበሩን ክብርና ህልውና ሊያናጋ የሚችል ተግባር ላይ መሳተፍ የለባቸውም

### መመሪያ ሁለት

### የስራ ግንኙነትን በተመለከተ

2.1.አባላት የያዙትን ወይም ሊሰሩት የፈለጉትን ስራ በተመለከተ ለሚመለከተው የስራ አቅራቢ ድርጅትን ሃላፊ ወይም ባለሙያ ውሳኔ ሊቀይር የሚችል ምንም አይነት ክፍያ ወይም መደለያ መስጠት የለባቸውም፡፡

2.2. አባላት ከአንድ ደንበኛ ጋር ሥራ ለመጀመር ወይም ለመቀበል ወይም ሥራ ለመቀጠል ምንም አይነት ኮሚሽን፤ ስጦታ ወይም ሌሎችን ከአቅም ወይም ብቃት ጋር ያልተያያዙ ማማለያ ዘዴዎች መጠቀም የለባቸውም፡፡

2.3. አንድ አባል በተጠና አግባብ ሌላውን አባል ከገበያ ለማስወጣት መንቀሳቀስ የለበትም

2.4. አንድ አባል በሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም ሌሎች በሚመለከታቸው አካላት ተገቢ እንዳልሆነ በተደነገገ የሂሳብ ስራ ወይም ኦዲት አገልግሎት አሰጣጥ የውድድር ዘይቤ ውስጥ መግባት የለበትም፡፡

2.5. አንድ አባል የአገልግሎት ስጠኝ ጥያቄ ከአዲስ ደንበኛ በሚቀርብለት ጊዜ እና ደንበኛው የሌላ አባል ደንበኛ እንደሆነ ካወቀ ጉዳዩን ለዚሁ አባል በቃል ማሳወቅ አለበት፡፡

2.6. አንድ አባል የሌላውን አባል ወይም በዘርፉ ላይ የተሰማራ ድርጅት ሥራ ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ በሌለበት ሁኔታ ማጣጣል የለበትም፡፡

2.7. አባላት የሚሰሩት ሥራ በዋና ጽ/ቤታቸውም ይሁን ቅርንጫፍ ጽ/ቤታቸው በሚመለከተው ባለሙያ እየተሰራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2.8. አንድ አባል ፈቃዱን ካላሳደሰ ሌላ ድርጅት ጋር በአጋርነት ወይም በተባባሪነት መስራት የለበትም፡፡

2.9. አንድ አባል በዚህ ወይም በሌላ አግባብነት ባለው መመሪያ ባልተጠቀሰ ሁኔታ ሙያዊ ወይም የግል ጥቅም ግጭት ውስጥ ቢገባ ራስን ከጉዳዩ ማግለል ወይም ግጭቱን ከምንጩ ማድረቅ ወይም ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

2.10. አንድ አባል ከደንበኛው ጋር ባለው የስራ ውል በታማኝነቱ ላይ ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል የቢዝነስ ፍላጎት ሲያጋጥመው ለደንበኛው በግልፅ ማሳወቅ አለበት፡፡

## መመሪያ ሦስት

## የአገልግሎት አሰጣጥ

**3.1.አባላት ደንበኞቻቸውን በብቃት ፣የሙያ ስነ ምግባርን በተላበሰ እና አድሎ በሌለበት ሁኔታ አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡**

3.1.1.አባላት አገልግሎታቸውን በብቃት እና ከደንበኞቻቸው ጋር በተስማሙበት ጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራውን አጠናቀው ማስረከብ አለባቸው፡፡

3.1.2. አባላት በስራ እንቅስቃሴያቸው ወቅት የሚፈጠርን የጥቅም ግጭት ማስወገድ፤ በነርሱ አቅም ለማስወገድ የማይችሉ ከሆነ ለማህበሩ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

3.1.3. አባላት ከደንበኞች ለተቀበሉት ስራ አጠቃላይ ሁኔታ እውነተኛ እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ለደንበኞቻቸው ማሳወቅ አለባቸው፡፡

3.1.4. አባላት በደንበኞቻቸው የተሰጣቸውን አመኔታ መጠበቅ አለባቸው፡፡

## 3.2. የቢሮ አደረጃጀት እና የስራ ሂደት

3.2.1. አባላት ለአጋሮቻቸውና ሰራተኞቻቸው የተመቻቸ የስራ ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር እና የአቅም ግንባታ እድሎችን ማመቻቸት አለባቸው፡፡

3.2.2 .አባላት በሚሰጡት አገልግሎት ዙሪያ ተገቢው ሥልጠና እና ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

3.2.3. አባላት የሚሰጡት አንድ አገልግሎት ከሌላኛው አገልግሎታቸው ወይም ንግዳቸው ጋር የሚጋጭ ከሆነ አገልግሎቱን መስጠት የለባቸውም፡፡

3.2.4. አባላት በየትኛውም አይነት ኮንትራት ከደንበኞች ጋር ለመስራት በሚስማሙበት ጊዜ የሚመለከተውን የሀገሪቱን (የኢትዮጵያን) ህግ የተከተለ እና አስፈላጊ መስፈረቶችን ያሟላ የውል ስምምነት ሰነድ ሊይዙ ይገባል፡

3.3. የሂሳብ ወይም ኦዲት ስራ

3.3.1. አንድ አባል ያለ ደንበኛው እውቅና ወይም ስምምነት በምንም አይነት ምክንያት በነፃም ይሁን በኮሚሽን ስራውን ለሌላ ተመሳሳይ ድርጅት አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

3.3.2. አንድ አባል አብሮ ከሚሰራው አጋር የገንዘብ ብድር አለበት በሚል የአጋሩን ሰነድ ወይም ቁሳቁስ ያለ አጋሩ ሥምምነት መውሰድ የለበትም፡፡

3.3.3. አባላት ስለስራቸው ሙያዊ ብቃት በሚገልጹበት ጊዜ የሌላቸውን ወይም እውነት ያልሆነውን ነገር መናገር ወይም ማስተዋወቅ የለባቸውም፡፡

3.3.4. አባላት ድርጅታቸውን በሚያስተዋውቁበት ጊዜ ተገቢና እውነት በሆነ ፤አዳማጩን በማያሳስት ወይም የተዛባ ግንዛቤ በማይሰጥ መልኩ ወይም ሙያዊ አመኔታ በማያሳጣ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 3.4. የምክር አገልግሎት

3.4.1. አባላት ለደንበኞቻቸው የሚሰጡትን የምክር አገልግሎት በሂሳብ ወይም ኦዲት ስራው መጨረሻ ስለሚያገኘው ውጤት የተሳሳተ መረጃ መስጠት ወይም የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል ያወጣውን የአሰራር ደንብ ወይም የስነ ምግባር መመሪያ እንዲሁም ይህንን መመሪያ በሚጥስ መልኩ አስቀድመው የሂሳብ ወይም ኦዲት ስራውን ውጤት መንገር የለባቸውም፡፡

3.4.2. አባለት ደንበኞቻቸው በሚስጥር እንዲይዙላቸው የጠየቋቸውን መረጃ በዚህ ስነ ምግባር መመሪያ ወይም በሌላ የሚመለከተው አካል በወጣ ህግና ደንብ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር ለሌላ አካል መንገር ወይም ማሳወቅ የለባቸውም፡፡

3.4.3. አባላት ደንበኞቻቸው የትኛውንም የሂሳብ ዘርፍ ህግ ጥሰው እየሰሩ ስለመሆኑ ካወቁ እና የህግ ጥሰቱ የህዝብና መንግስት በአጠቃላይ የሌላን ወገን ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ሲገነዘቡ ደንበኛውን ከአድራጎቱ እንዲቆጠብ ሊመክሩት፣ ምክራቸውን ካልተቀበለ ስራውን ተቀብለው ከመስራት ሊታቀቡ እና ለሚመለከተው አካል ሊያሳውቁ ይገባል፡፡

3.4.4. አባላት ሊያውቁ ሲገባቸው ባለማወቃቸው ወይም እያወቁ የደንበኛቸውን ህገ-ወጥ ስራ ወይም ስነ ምግባር እንዲቀጥል መምከር ወይም መደገፍ የለባቸውም

## 3.5. በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል መስራት

አባላት በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ያለን አንድ ስራ ሲሰሩ ስራውን በገለልተኝነት መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡

## *መመሪያ አራት*

## *የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ*

4.1. አንድ አባል የአንድን ደንበኛ የስራ አይነት እና መጠን በተመለከተ በቂ መረጃ ሳይኖረው እና በደንበኛው ሳይጋበዝ ወይም ሳይጠየቅ የአገልግሎት ዋጋ ተመን ሊያወጣ አይችልም፡፡

4.2. አንድ አባል የአገልግሎት ዋጋ በሚያወጣበት ጊዜ የሌላን አባል ዋጋ እንደ መነሻነት መጠቀም አይችልም፡፡

4.3. አባላት ለወደፊት እንደአስፈላጊነቱ በማህበሩ በሚዘጋጀው የዋጋ ወለል እና ጣሪያ ላይ ተመስርተው ዋጋ ሊያወጡ ይገባል፡፡

## *መመሪያ አምስት*

## *ድርጅትን ለማስተዋወቅ እና ተቀባይነት ለማግኘት መስራት*

5.1. አባላት ሙያዊ ተቀባይነት ማግኘት የሚገባቸው በሚሰጡት አገልግሎት ጥራት እና ቅልጥፍና ሲሆን ለሌሎች በዘርፉ ለተሰማሩ ድርጅቶች እውቅና እና የሚገባቸውን አክብሮት ሊሰጡ ይገባል፡፡

5.2. አባላት ከደንበኞች ከሚሰጣቸው ስራ ጋር በተያያዘ ለስራው የሙያ ብቃት እና ልምድ የተዛባ፣ የሚያሳስት ወይም የተጭበረበረ ገለፃ መስጠት የለባቸውም፡፡

## መመሪያ ስድስት

## ጠቅላላ ግዴታዎች

### 6.1. ሙያዊ ግዴታዎች

6.1.1. አባላት የሙያ ተአማኒነት (ተቀባይነት) እና ክብር መጠበቅ አለባቸው፡፡

6.1.2. አባላት ክህሎትና እውቀታቸውን ለማሳደግ መጣር አለባቸው

6.1.3. አባለት የሙያውን ጥራት ደረጃ ለማሳደግ መጣር አለባቸው

6.1.4. አንድ አባል ሌላ አባል ወይም ሌላ በዘርፉ የተሰማራ ባለሙያ ይህንን ወይም ሌላ ስለዘርፉ የተዘጋጀ የስነ ምግባር መመሪያ እየጣሰ እንደሆነ በቂ መረጃ ካለው ጉዳዩን ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

6.1.5. አባላት በራሳቸው ባልተሰራ ወይም ሃላፊነት ሊወስዱበት በማይችሉት የሂሳብ ወይም የኦዲት ስራ ላይ መፈረም ወይም ማህተማቸውን ማድረግ ወይም አሳልፈው በመስጠት ሌሎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ የለባቸውም፡፡

6.1.6. አባላት ለቀጠሯቸው ሰራተኞች ወይም አጋር ድርጅቶች ወይም ለደንበኞቻቸው ተገቢውን ክብር እና እውቅና መስጠት አለባቸው፡፡

### 6.2. ማህበራዊ ግዴታዎች

6.2.1. አባላት በግል እና በሙያ እንቅስቃሴያቸው ወቅት የማህበረሰቡን ጥቅም ማስተዋወቅ፣ ማገልገል እንዲሁም ከሙያቸው ጋር ተያይዘው የወጡ ህጎችን ተከትለው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

6.2.2. አባላት ለሙያቸው ማህበራዊ አገልግሎት መስጠት እና ሰራተኞቻቸዉንም ተመሳሳይ አገልግሎት እንዲሰጡ ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡

6.2.3. አባላት በሲቪክ እና በሙያተኞች እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ፤ ስለሂሳብ ስራ ጥቅም እና ምንነት የሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች ሃላፊነት እና የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ምን እንደሆኑ ማህበረሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ መጣር አለባቸው

6.2.4. አባላት በሙያ እንቅስቃሴያቸው ወቅት የሰዎችን ሰብአዊ መብት ማክበር እና ለማስከበር መጣር አለባቸው።

6.2.5. አባላት ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት፤ በግንኙነታቸው ወይም በስራቸው ላይ ተፅዕኖ ሊፈጠር የሚችል ምንም አይነት ክፍያ ወይም ስጦታ መቀበል የለባቸውም

6.2.6. አባላት የሌሎችን መብት በሚጋፋ አላስፈላጊ በሆነ ወይም በማታለል ድርጊት ላይ መሳተፍ የለባቸውም።

6.2.7. አባላት ሀይማኖትን፣ ዘርን፣ ፆታን፣ አካባቢን፣ እድሜን እና አቅምን ወዘተ መሰረት ያደረገ ሙያዊ አድሎ መፈፀም የለባቸውም።

4. <u>የመመሪያው አፈፃፀም</u>

**1. የዲሲፕሊን እርምጃ ቀጥሎ በተገለጹት ሁኔታዎች ሊከሰት ይችላል፤**

1.1. ይህን እና የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ያወጣውን የስነ ምግባር መመሪያ አለመተግበር

1.2. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መጣስ

1.3. ማህበሩን ጥቅም እና ክብር ሊያሳጣ የሚችል ተግባር መፈፀም

1.4. የሙያ ደረጃውን የሚያጎድፍ ወይም ዝቅ የሚያደርግ ተግባር መፈፀም

1.5. የሙያ ደረጃው የሚጠይቀውን ተገቢ የሆነ ሙያዊ ጥንቃቄ፣ ክህሎት እና ብቃት ተግባራዊ አለማድረግ

2. <u>የሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች በቅደም ተከተል</u>

1. በመጀመሪያ የቃል ማስጠንቀቂያ እና ተግሳፅ

2. ለሁለተኛ ጊዜ ሲያጠፋ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ

3. ለሶስተኛ ጊዜ ሲያጠፋ ከማህበር አባልነት መሰረዝ እና ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ እና ለሌሎች አጋር አካላት ማሳወቅ

3. <u>አስፈፃሚ</u>

ይህ የስነ ምግባር መመሪያ ተግባራዊ ሆኖ ሁሉም አባላት በህግና ደንብ እንዲመሩ ለማስቻል ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ከክልል እስከ ወረዳ ባለው የማህበሩ አደረጃጀት ሁሉም አመራር እና አባላት የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

ሆኖም አንድ ሃላፊነት ተሰጥቶት የሚሰራ አካል መኖር ስላለበት በክልል እና በዞን ደረጃ የአባላት ዲሲፕሊን ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፡፡ የሃላፊነት ገደብ እና የስራ ዝርዝርም በክልሉ የማህበር ስራ አመራር ተቀርፆ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡